# ለቦርድ ግንዝቤ የሚቀርቡ የደወል ሰአቶች አማራጮች ማጠቃለያ

ROCKVILLE, MARYLAND

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በየእለቱ ትምህርት ዘግየት ብለው እንዲጀምሩ የሚያስችሉ በርካታ አማራጮችን በማገናዘብ ላይ ይገኛል። ቦርዱ በጃንዩወሪና በፌብሩዋሪ መጀመርያ ላይ በአማራጮቹ ላይ የህዝብ አስተያየቶችን ይሰበስባል። ማንኛቸውም ለውጦች፣ የ2016 የስራ ማስኬጃ በጀት ጥያቄ አካል በመሆን፣ ፌብሩዋሪ 10፣ 2015 ይፀድቃሉ።

## መነሻ

የወቅቱ መጀመርያና መጨረሻ ጊዜዎች—ወይም የደወል ጊዜዎች—ለMCPS የሚከተሉት ናቸው፡-

| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
|---|---|---|
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡25 a.m.- 2፡10 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡55 a. m. - 2፡40 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 8፡50 a.m.-3፡05 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 9፡15 a.m.-3፡30 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |

በ2013፣ Superintendent Joshua P. Starr፣ ቀደም ብሎ ትምህርት መጀመር በልጆች ላይ ስለሚያስከትለው ተፅእኖ እያደገ ከመጣው ምርምር ምክንያት፣ የትምህርት መጀመርያና ማብቂያ ሰአቶችን የማሸጋሸግ ሁኔታ የሚያጠና የደወል ጊዜያቶች የስራ ቡድን (Bell Times Work Group) ፈጠረ። የስራ ቡድኑ ዘገባ ኦክቶበር 2013 ይፋ ሆነ፣ ከውጤቶች በመነሳትም፣ Dr. Starr የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን መነሻ ጊዜዎች በ50 ደቂቃዎች እንዲዘገይ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ10 ደቂቃ ቀደም እንዲል፣ የኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች የትምህርት ቀን ግን መጀመርያ ሰአታቸው ሳይቀየር በ 30 ደቂቃዎች መራዘሙ እንዲገናዘብ ሃሳብ አቀረበ።

Montgomery County Public Schools (MCPS) የዚህን ሃሳብ ፋይናንስያዊ ተፅእኖ በጠቅላላ አጠና እናም ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ ወላጆችን፣ የማህበረሰብ አባላት፣ እና ቢዝነሶችን ከሚያካትት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው በርካታ አካላት ሰፊ አስተያየቶችን ሰበሰበ። በጁን 2014፣ ግምት ከሚሰጠው አመታዊ ወጪ—ቢያንስ $21 ሚልዮን በአመት—እና ከህብረተሰቡ ከተገኘ የተወዛገበ ድጋፍ በመመስረት፣ Dr. Starr MCPS በቀረበው ሃሳብ እንዳይገፋበት አሳሰበ።

## ተጨማሪ አማራጮች

የትምህርት ቦርድ በአመት ከ$10 ሚልዮን በላይ የማያወጡ የደወል ሰአቶች መለወጫ አማራጮች እንዲያዳብር የበላይ ተቆጣጣሪውን ጠይቆታል። እነዚያ አማራጮች ጃንዋሪ 6፣ 2015 ይፋ ሁነዋል። የአማራጮቹ አጭር መግለጫ ከዚህ በታች ይገኛል። ስለ እነዚህ አማራጮችና የአሰራርና የፋይናንሳዊ ተፅእኖአቸው የተሟላ ዘገባ ለማንበብ፣ የMCPSን ድርጣብያ— www.montgomeryschoolsmd.org—ይጎብኙና "bell times"ን ፈልጉ።

በነዚህ የቀረቡት ሀሳቦች ዋጋ በስተጀርባ አንቀሳቃሹ ታሳቢ ትራንስፖርት ነው። ቀልጣፋና ኤኬኖሚያዊ የትራንስፖርት ስርአት ለማካሄድ፣ አብዛኛዎቹ የMCPS አውቶቡሶች ጥዋትና ማታ አራት ዙሮች መፈፀም አለባቸው። የት/ቤት መጀመርያና መጨረሻ ሰአቶች አውቶቡሶች አንድ መሰመር ፈፅመው ወደሚቀጥለው ለመድረስ እንዲችሉ በቂ ጊዜ እንዲሰጧቸው ያስፈልጋል። ቦርዱ የሚያገናዝበው እያንዳንዱ አማራጭ የትራንስፖርትን ዋጋዎች በተለያየ ሁኔታ ተፅእኖ ያደርግባቸዋል። የተውሰኑ ምንም የፋይናንስ ተፅእኖ አይኖርባቸውም፣ ሌሎች ግን የትራንስፖርት ዋጋዎችን ይጨምራሉ።

## በበላይ ተቆጣጣሪ የቀረበ

አዲሱን ዘገባ ሲገመግም፣ በመጀመርያ ሰአቶች መለወጥ ላይ ሊገፋበት ቦርዱ ከፈለገ በMCPS ስራ ማስኬጃ በጀት ላይ ተጨማሪ ዋጋ የማያስከትሉትን አማራጮች ብቻ እንዲያገናዝብ Dr. Starr ያሳስባል። ይህ ሃሳብ የተደረገው በስቴትና በካውንቲ ወኪል በጀቶች መቀነስ የሚያስከትሉ ትርጉም ያዘሉ የገቢ ቅናሾች አሉ የሚል ከካውንቲ ከመነጨ ወሬ በመነሳት ነው።

## አስተያየት ማቅረብ

ቦርዱ በአማራጮቹ አስተያየቶችን ለመስማት፣ ሀሙስ፣ ጃንዩወሪ 22፣ 2015፣ በCarver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive in Rockville አዳራሽ ውስጥ ሁለት የህዝብ ችሎቶች ያከናውናል። የመጀመርያው ችሎት ከ3:30 እስከ 5:30 p.m. ሁለተኛው ደግሞ ከ6:30 to 9:30 p.m. ይካሄዳሉ። በችሎቱ ተገኝተው ለመመስከር ለመመዝገብ፣ እባክዎን በ301-279-3617 ጃንዩወሪ 15፣ 2015 ከ9 a.m. በኋላ ጥሪ ያድርጉ። ሁሉም ተናጋሪዎች ሶስት ደቂቃዎች ይኖራቸዋል። የፅሁፍ ሃሳብ/አስተያየት ወደ belltimes@mcpsmd.org መላክ ይቻላል፣ እናም ከሰኞ፣ ፌብሩዋሪ 2፣ 2015 በፊት መድረስ አለባቸው።

**አማራጭ 1— ሁሉንም የመጀመርያ ሰአቶች ከ 20 ወይም 30 ደቂቃዎች ማዘግየት፡-** ይህ አማራጭ ተማሪዎች ወደ ት/ቤት የሚሄዱበትን ቅደም-ተከተል አይቀይርም የትምህርት ቀን/ሰአቶችንም አይለውጥም። ይህ አማራጭ የሚያስከትለው ፋይናንሳዊ ተፅእኖ ጥቂት ነው።

| ደረጃ | 20 ደቂቃዎች ዘግይቶ መጀመር | 35 ደቂቃዎች ዘግይቶ መጀመር |
|---|---|---|
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡45 a.m.–2፡30 p.m. | 8:45 a.m.–2:00 p.m. |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 8:15 a.m.–3:00 p.m. | 8፡30 a.m.–3፡15 p.m. |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 9:10 a.m.–3:25 p.m. | 9:25 a.m.–3:40 p.m. |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 9:35 a.m.–3:50 p.m. | 9:50 a.m.–4:05 p.m. |

**አማራጭ 1a—ሁሉንም የመጀመርያ ሰአቶች ወደኋላ ማሸጋሸግ፡-** በጃንዩወሪ 13፣ 2015፣ የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ከአማራጭ 1 ጋር ተመሳሳይ የሆነ አንድ አማራጭ ጨመረ። የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከ20 ወይም ከ35 ደቂቃዎች በኋላ ይጀመራሉ፣ በሌላ በኩል የኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች ከ10 ወይም ከ25 ደቂቃዎች በኋላ ይጀምራሉ። ይህ አማራጭ የኤሌሜንታሪ ት/ቤትን የትምህርት ቀን በ10 ደቂቃዎች አራዝሞ 6 ሰአቶችና 25 ደቂቃዎች ያደርገዋል። ተጨማሪዎቹ 10 ደቂቃዎች ለምሳ ወይም ለእረፍት አገልግሎት ይውላሉ። የዚህ አመራጭ ፋናንሳዊ ተፅእኖ በመወሰን ላይ ይገኛል።

| ደረጃ | MS/HSን (መካከለኛ/ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን) በ20 ደቂቃ አዘግይቶ ማስጀመር | MS/HSን (መካከለኛ/ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን) በ35 ደቂቃ አዘግይቶ ማስጀመር |
|---|---|---|
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡45 a.m.–2፡30 p.m. | 8:45 a.m.–2:00 p.m. |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 8:15 a.m.–3:00 p.m. | 8፡30 a.m.–3፡15 p.m. |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 9:00 a.m.–3:25 p.m. | 9:15 a.m.–3:40 p.m. |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 9:25 a.m.–3:50 p.m. | 9:40 a.m.–4:05 p.m. |

**አማራጭ 2—መጀመርያ ኤሌሜንታሪ ት/ቤቶችን ማስጀመር፡-** ይህ አማራጭ አራት የተለያዩ ሞዴሎች አሉት፣ የተወሰኑት በትምህርት ቀን/ሰአቶች አነስተኛ ለውጦች ብቻ በመጠየቅ።

| የኤሌሜንታሪ ት/ቤት መጀማርያ ማስጀመር፣ ሞዴል 1፣ በአመት $2.6 ሚልዮን | | |
|---|---|---|
| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 7:35 a.m.–1:50 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 8:15 a.m.–2:00 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 8:45 a.m.–3:30 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 9:15 a.m.–4:00 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |

| የኤሌሜንታሪ ት/ቤት መጀማርያ ማስጀመር፣ ሞዴል 2፡- በአመት $5.2 ሚልዮን | | |
|---|---|---|
| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 8:00 a.m.–2:15 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 8:25 a.m.–2:40 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 9:10 a.m.–3:55 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 9:40 a.m.–4:25 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |

| የኤሌሜንታሪ ት/ቤት መጀማርያ ማስጀመር፣ ሞዴል 3፣ በአመት $4.55 ሚልዮን | | |
|---|---|---|
| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 7፡45 a.m.-2፡05 p.m. | 6 ሰአት፣ 20 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 8:15 a.m.–2:35 p.m. | 6 ሰአት፣ 20 ደቂቃ |
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 8፡50 a.m.-3፡35 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 9:30 a.m.–4:05 p.m. | 6 ሰአት፣ 35 ደቂቃ |

| የኤሌሜንታሪ ት/ቤት መጀማርያ ማስጀመር፣ ሞዴል 4፣ በአመት $3.9 ሚልዮን | | |
|---|---|---|
| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 7፡45 a.m.-2፡10 p.m. | 6 ሰአት፣ 25 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 8:15 a.m.–2:40 p.m. | 6 ሰአት፣ 25 ደቂቃ |
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 8፡50 a.m.-3፡35 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 9:30 a.m.–4:05 p.m. | 6 ሰአት፣ 35 ደቂቃ |

**አማራጭ 3—የDr. Starr በየኦክቶበር 2013 የቀረበ ሀሳብን ማሻሻል፡-** ይህ አማራጭ ሁለት የተለያዩ ሞዴሎች አሉት፣ ከነዚህም አንዱ ለተወሰኑ ተማሪዎች የተወሰነ የትምህርት ቀን/ሰአቶች ለውጥ ይጠይቃል።

| የDR. STARR በመጀመርያ የቀረበ ሀሳብ፡ በአመት ወደ $21 ሚልዮን አካባቢ (ግንዛቤ ውስጥ ያልገባ) | | |
|---|---|---|
| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡45 a.m.–2፡30 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 8:15 a.m.–3:00 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 8፡50 a.m.–3፡35 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 9:15 a.m.–4:00 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |

| የDR. STARR በቅድሚያ የቀረበ ሀሳብ፡- የተሻሻለ ሞዴል 1፡- በአመት $5.2 ሚልዮን | | |
|---|---|---|
| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡35 a.m.–2፡20 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 8:15 a.m.–3:00 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 9፡20 a.m.–3፡35 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 9:45 a.m.–4:00 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |

| የDR. STARR በቅድሚያ የቀረበ ሀሳብ፡- የተሻሻለ ሞዴል 2፡- በአመት $5.85 ሚልዮን | | |
|---|---|---|
| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 7:30 a.m.–2:00 p.m. | 6 ሰአት፣ 30 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 8:00 a.m.–2:25 p.m. | 6 ሰአት፣ 25 ደቂቃ |
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 8:45 a.m.–3:30 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 9:30 a.m.–3:55 p.m. | 6 ሰአት፣ 25 ደቂቃ |

**አመራጭ 4—የሁለተኛ ድረጃን የትምህርት ቀን ወደ ሁለት መክፈል፡-** ይህ አማራጭ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሁለት የተለያዩ የመጀመርያና የመጨረሻ ጊዜ ይኖረዋል፣ ዘግይተው ለመጀመር ለሚፈልጉ ተማሪዎች የትራንስፖርት አማራጭ አይቀርብም። የዚህ አማራጭ ዋጋ ገና ለወደፊት የሚወሰን ነው።

| ደረጃ | ጊዜ | የትምህርት ቀን/ሰአቶች ርዝመት |
|---|---|---|
| የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ1ኛ ፔርየድ መጀመርያ | 7፡25 a.m.- 2፡10 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ3ኛ ፔርየድ መጀመርያ ምንም ትራንስፖርት አይቀርብም | 9:05 a.m.–3:50 p.m. | 6 ሰአት ፣ 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡55 a.m.–2፡40 p.m. | 6 ሰአት፣ 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 8፡50 a.m.–3፡05 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 9፡15 a.m.–3፡30 p.m. | 6 ሰአት፣ 15 ደቂቃ |

**አማራጭ 5—የደውል ሰአቶችን ሳይለውጡ መቀጠል፡-** ይህ አማራጭ የማንኛውንም ት/ቤት የመጀመርያ ወይም የመጨረሻ ሰአቶች አይለውጥም፣ ቢሆንም፣ እንደ አጫጭር ፕሮግራሞች እና የመስመር ላይ ኮርሶችን በተጨማሪ ማቅረብን የመሳሰሉ፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በተጨማሪ ለመተኛት የሚያስችላቸው ማሻሻያዎችን ይዳስሳል።



MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND
0890.15 • EGPS • AMHARIC